በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የመ.ቁ.241180

ጥቅምት 29/2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡-ወ/ሪት ፌቨን ፈድሉ - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡1. ወ/ሮ አይሻ ከድር

2. ወ/ሮ ኢማን ሲራጅ ጠ.አቶ አብርሃም ባህረ - ቀርበዋል

3. ወ/ሪት ከድጃ ፈድሉ

4. ሀፃን ፍዘኪር ፈድሉ

5. አቶ ፉአድ ፈድሉ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍርድ

ጉዳዩ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ አቤቱታን መሰረት አድርጎ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/282268 ላይ ታህሳስ 06/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች ጥር 20/2013 ዓ.ም ጽፈው ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ በአቤቱታቸውም ወላጅ አባታቸው ሟች አቶ ፈድሉ ኑርጋ የካቲት 24/1994 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ምክንያት ወራሽነታቸውን በፍርድ ቤት ያረጋገጡ መሆኑን፤ ሟች በህይወት እያሉ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 11 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥር 1676 የሆነ መኖሪያ ቤት እና የሚከራዩ በርካታ ክፍሎችን ያፈሩ መሆኑን በመግለፅ የሟቹ የውርስ ሀብት እንዲጣራላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በአቤቱታው ላይ የአሁን ተጠሪዎችን መከራከሪያ ከሰማ በኋላ የውርስ አጣሪ ሹሞ ውርሱም ተጣርቶ ጥቅምት 16/2014 ዓ.ም የተፃፈ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ በቀረበው ሪፖርት ላይ የግራ ቀኙን መከራከሪያ ከሰማ በኋላ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በውሳኔውም በአመልካች እና ተጠሪዎች መካከል ሰኔ 03/2013 ዓ.ም በተደረገ የድርሻ ክፍፍል ስምምነት መሰረት አመልካች በሞግዚታቸው በኩል የድርሻ ክፍፍል ስምምነት ያደረጉ በመሆኑ ስምምነቱ ባልፈረሰበት ሁኔታ በዚህ መዝገብ የውርስ ሀብት ተብሎ ሊመዘገብ የሚገባ ንብረት የለም በማለት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአሁን ተጠሪዎችን አስቀርቦ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በሞግዚት አማካኝነት የተደረገው ስምምነት ፈራሽ ነው አይደለም የሚለው ጉዳይ በሌላ መዝገብ የሚታይ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቱ ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ጥር 23/2015 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈጽሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች አስቀድመው ድርሻቸውን በስምምነት ወስደዋል በሚል መነሻነት አቤቱታቸው

ውድቅ የተደረገበት አግባብ በዚህ ችሎት እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪ ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንግዲህ የሚችን የውርስ ሀብት ማጣራት አስፈላጊ ከሚያደርጉት በርካታ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ በውርስ ሊተላፍ የሚችል የሚችን የውርስ ሀብት እና የውርሱ ተቀባይ እነማን እንደሆኑ መለየት እንደሆነ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 944 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሚች የውርስ ሀብት የሆነውን ንብረት አንጥሮ ለመለየትም ደግሞ በማጣራት ሂደቱ ውስጥ የንብረቱን የውርስ ሀብት መሆን አለመሆን አስምልክቶ በሚነሱ ክርክሮች ላይ ሂደቱን በሚመራው ፍርድ ቤት ማስረጃን መሰረት ያደረገ ውሳኔ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ከማጣራቱ በኋላ ለውርሱ ተገቢ የሆኑት አካላት ለሚያቀርቡት የድርሻ ክፍፍል ጥያቄም መሰረት የሚሆነው ይኼው ስለመሆኑ የውርስ ሀብት ክፍያን አስምልክቶ በፍ/ብ/ህግ ከቁጥር 1062-1064 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

የሚቹ ወራሾች ማንነት እና የውርስ ሀብቱ ምንነት ተለይቶ የሚታወቅ ከሆነ በህጉ በተመለከተው አኳኋን የውርስ ሀብትን ማጣራት ግዴታ አይደለም፡፡ የሚች የውርስ ሀብት በህጉ በተመለከለተው አግባብ ተጣራም አልተጣራም የውርስ ንብረት ክፍፍል አሰራር በወራሾች መካከል በሚደረግ ስምምነት፣ በወራሾቹ መካከል ስምምነት ከሌለ ደግሞ ከእነርሱ መካከል አንዱ ተግቶ ያሰናዳውን የክፍያ ሐሳብ ለዳኞች አቅርቦ በማፀደቅ ሊፈፀም እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1079 1080 ድንጋ ያስገነዝባል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የሚች የውርስ ሀብት ክፍፍልን አስምልክቶ ሰኔ 03/2010 ዓ.ም የተፈረመ ስምምነት ስለመኖሩ በግራ ቀኙ የተካደ አይደለም፡፡ በአመልካች በኩል እየቀረበ ያለው መከራከሪያ ስምምነቱ በሞግዚት በኩል የተደረገ ሆኖ በህግ ለሞግዚ ከተሰጠው ስልጣን በላይ የተደረገ በመሆኑ በህግ ፊት አይፀናም የሚል ነው፡፡ እንደተባለው ስምምነቱ በህግ ፊት የሚፀና መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ ስምምነቱን አስምልክቶ እራሱን ችሎ በሚቀርብ ክርክር የሚወሰን ይሆናል፡፡ በዚህ መልኩ ክርክር ተደርጎ ስምምነቱ አይፀናም ባልተባለበት ሁኔታ

የተፈረመው ስምምነቱ መሰረት የተደረገው ክፍፍል ወደ ጎን ተትቶ የሚች የውርስ ሀብት እንደአዲስ የሚጣራበት የህግ አግባብ የለም፡፡ በስምምነቱ መሰረት የአሁን አመልካች የደረሳቸው ድርሻ ምን ውጤት ይኖረዋል የሚለውም ከስምምነቱ ህጋዊነት በኋላ አቋም የሚወሰድበት ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/282268 ላይ ታህሳስ 06/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !